# መሪዎችን ማሳደግ

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገረ መለኮት

# መግቢያ

©2023 HTTP


## የእኛ ዓላማና መዋቅር

መሪዎችን የማሳደግ አውደ ጥናት ማለት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን መሪዎች የማሰልጠን መርሐግብር ነው። አርማው የትምህርቱን አካሄድ ይወክላል። በአርማው ላይ ስድስት ተሽከርካሪ ነገሮች አሉ። ስድስቱም ተሽከርካሪ ነገሮች ስድስት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ይወክላሉ። ሦስቱ ተሽከርካሪዎች ከብሉይ ኪዳን ሦስት ክፍሎችን ያመለክታሉ። እነዚህም ሕግ ፤ ነቢያት እና ጽሑፎች ናቸው። ከጽሑፎች ውስጥ ትልቁ መዝሙረ ዳዊት በመሆኑ ምክንያት አንዳንድ ጊዜ ጽሑፎቹ መዝሙረ ዳዊት በመባል ይታወቃሉ። ሌሎች ሦስቱ ተሽከርካሪዎች ደግሞ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍትን የሚወክሉ ሲሆን እነዚህም የታሪክ መጽሐፍት (አራቱ ወንጌላትና የሐዋሪያት ሥራን ያካትታል)፣መልዕክቶች (እነዚህ ደግሞ ለአብያተክርስቲያናት ወይም ለግለሰቦች የተጻፉ ደብዳቤዎች ሁሉ ማለት ነው) እና የራዕይ መጽሐፍ። እነዚህ ስድስቱ ክፍሎች ሁሉም ጠቃሚዎች ናቸው ስለዚህ ሊጠኑና ሊሰበኩም ይገባል።

መሪዎችን የማሳደግ አውደ ጥናት ግቡ በቤተክርስቲያን ወስጥ ያሉትን መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል በመረዳት እና በመውደድ እንደዚሁም ደግሞ እንደየ ተሰጣቸው ፀጋ በማስተማር ፣በመስበክና በማሰልጠን የእግዚአብሔርን ቃል ለመጠቀም እንዲችሉ መርዳት ነው። መሪዎችን የማሳደግ አውደ ጥናት ተሳታፊዎች ስድስት የተለያዩ ጊዜያት ያህል በአንድ ላይ ይገናኛሉ። በተገናኙ ቁጥር ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ከስድስቱ ክፍሎች አንዱን ያጠናሉ። እንደዚሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ከእያብዳንዱ ክፍል ስፋት የተነሳ በሚሰበሰቡበት ጊዜ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ያለውን ዋና ዋና ጭብጦች፣ ታሪኮች፣የመጽሐፎቹን በህሪያት ይዳስሳሉ።

ጊዜ ሲኖር ደግሞ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች “ትልቅ ስዕል” አጠቃላይ ዕይታ ከዚያ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ካለው ጥልቅ ትምህርት ጋር በማዛማድ ይመለከታሉ። ለምሳሌ ያህል ስለሕጉ በአጠቃላይ ማስተማርን ከሕጉ አንድ ክፍል (ለምሳሌ ከዘፍጥረት ወይም ከዘዳግም ውስን ክፍል በመውሰድ) በጥልቀት ከሚጠናው ክፍል ጋር በማዛመድ መመልከት ሊሆን ይችላል። የሥልጠናው ሁለቱ ክፍሎች፣ ከተማን ከመመልከት ሁለት የተለያዩ ዘዴዎች ጋር ሊመሳሳል ይችላል። በመጀምሪያ፣ ሄሊኮፕተር ከላይ ሆኖ በአንድ ከተማ ላይ እያንዣበበ ወደ ታች እያየ እንደ ሚቃኝ ሁሉ እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጎላ ካለ ዕይታ አንጻር እንመረመራለን። ይህ “ትልቅ ስዕል” የሚለው አመለካከት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ለአንኳር ጭብጦች አንጻዖት የሚሰጥ ነው። በሁለተኛ ደረጃ በከተማ ውስጥ በእግሩ እየተራመደ የሚሄድ ሰው ሁሉንም ህንፃዎች ማየት እንደማይችል ነገር ግን በሚያልፍበት መንገድ ሁሉ ብዙ ጥቃቅን ዝርዝር ጉዳዮችን ማየት እንደሚችል ግለሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ አንዱ ክፍል በቅርበት እንመረምራል። አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጥልቅት ማጥናት በአንድ ከተማ ላይ ከላይ ወደታች ዕያየ እንደ ሚያንዣብብ ሄሊኮፕተር አይደለም።

ነገር ግን ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን እየተመለከተ በአንድ የከተማው ክፍል በእግሩ እንደሚራመድ ሰው ነው እንጂ። በሄሊኮፕተር ከላይ ሆኖ የሚያንዣብበው ሰው የከተማውን ብዙውን ክፍል ማየት ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን ደግሞ በአንዱ የከተማው ክፍል በእግሩ የሚጓዝው ሰው ደግሞ ተጨማሪ ጥቃቅን ዝርዝር ጉዳዮችን ማየት ይችላል።



## ፤. የእግዚአብሔር ቃል ምንድር ነው?

የእግዚአብሔር ቃል ለሰዎች ከእግዚአብሔር በቸርነቱ የተሰጠ ስጦታ ነው። ከተሀድሶ ዘመን ጀምሮ (ይህም በምዕራቡ አለም ባለችው ቤተክርስቲያን በ1500ዎቹ ግድም አካባቢ የተጀመረው የተሃድሶ ዘምን ማለት ነው) የፕሮቲስታንቱ አብያተ ክርስቲያናት *ቃል እግዚአብሔር ብቻ* በሚለው መርህ ያምናሉ። ይህም ደግሞ "መንፍስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስተምርበት ታላቁ የዕምነትና የተግባር መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው" የሚለው መርህ ነው፤ (ሮጀር ቲ. ቤክዊት ፣ የብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን እና የጥንት የአይሁድ እምነት ዳራ፣ ገጽ 5 ማጣቀሻ ይመልከቱ)። ስለዚህ ይህ ማለት የቤተ ክርስቲያን እምንትና ተግባር በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው ማለት ነው። እንግዲህ ቅዱሳት መጽሐፍት "የእምነትና የተግባር ታልቁ ሕግ" መሆናቸውን እውነት ከሆነ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የሥልጣን ምንጭ የሆኑትን መጽሐፍት ማወቅ ደግሞ አስፈላጊ ነው። ይህ በመለኮታዊ እስተንፋስ መሪነት የታጻፉት መጻሕፍት ዝርዝር *ቀኖና* ይባላል። ቀኖና የሚለው ከግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም "ደንብ" ማለት ነው።

ብሉይ ኪዳንን በተመለከተ በ1546 በትሬንት ብተደረገው ጉባኤ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስና የአዋልድ መጻሕፍት በእግዚአብሔር እስትፋስ የተጻፍ መሆናቸውን ገልጻ ነበር። ይሁን እንጂ ይህንን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውሳኔ ያልተቀበሉ የፕሮቲስታንት አብያተ ክርስቲያናት የዕብራይስጥ መጻሕፍ ቅዱስ መጻሕፍትን ብቻ ቀኖናዊ እንደሆኑ ሲቀበሉ የተቀሩት የአዋልድ መጻሕፍት በሙሉ ደግሞ ቀኖናዊ አይደሉም በማለት ሳይቀበሉዋቸው ቀርተዋል። የፕሮቲስታንት አብያተ ክርስቲያናት ለሙግታቸው እንደ መከራከሪያ የሚያንሱት፤ ቀኖና ብልው እውቅና የሰጡዋቸው መጽሐፍት በኢየሱስና በሐዋሪያትም ተቀባይነት ያገኙ መጽሐፍት ናቸው የሚል ነው።

ክርስቲያኖች **ቀኖና ተሟልቶአል ወይም ተዘግቶአል** ብልው ያምናሉ (የተዘጋው የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕል የዚህ ማስታወሻ ምሳሌ ነው)። እንግዲህ ከዚህ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም አዲስ መጻሕፍት አይታከሉም ማለት ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በነቢያት (ባለሥልጣን የሆነው ቃሎቻቸው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይገኛል) እና በሐዋሪያት ((ባለሥልጣን የሆነው ቃሎቻቸው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛል ) መሠረት ላይ እየተገነባች ነው።

> ከዚህ የተነሣ እናንተ ከቅዱሳን ጋር የአንድ አገር ዜጋ፣ የእግዚአብሔርም ቤተ ሰብ አባል ናችሁ እንጂ፣ከእንግዲህ ወዲህ መጻተኞችና እንግዶች አይደላችሁም። **በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት**

**ላይ ታንጻችኋል**፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይም ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ አንድ ላይ ተገጣጥሞ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል። **ኤፌሶን 2፡19–21።**

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 66 መጽሕፍት እና ወደ 40 የሚጠጉ ዳራሲዎች አሉ። እነዚህ ደራሲዎች ደግሞ ነገሥታት፣ ነቢያት፣ እረኞች፣ ቀራጮች እና ዓሣ አጥማጆች ነበሩ። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ቃሉን የጻፉት ብዙ የተለያዩ ሰዎች ቢሆኑም 66ቱ መጻሕፍት ግን የተያያዙ ናቸው። ድራሲዎቹ የጻፉት ስለራሳቸው ታሪኮች ወይም ሃሳቦች አይደለም (**2 ጴጥሮስ 1፡20–21** ይመልከቱ)። ሁሉንም የአንድ ታሪክ አካል ናቸው። በደራሲዎቹ የተጻፉ ቃላት ከእግዚአብሔር የመጡ ናቸው። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ ቅዱሳት መጽሕፍት "የእግዚአብሔር እስትንፋስ" እንደሆኑ ሊናገር የቻለው (**2 ጢሞቴዎስ 3፡14–17** ይመልከቱ)። መጽሐፍ ቅዱስ ከሰዎች ጥበብ የመጣ አይደለም። ይልቁንም "ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩት" እንጂ (**2 ጴጥሮስ 1፡19–21**)። ደራሲዎቹ የጻፍት ታዋቂ እንዲሆኑ ብለውም አይደለም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ህዝብ ለመርዳት አቅደው ነው እንጂ። ለዚህም ነው ጴጥሮስ፣ "እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገሉ ተገለጠላቸው" ያለው (**1 ጴጥሮስ 1፡12**)**።** ደራሲዎቹ የእግኢአብሔር መንፈስ ያለበትን ቃል ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲደርስ ጠንክረው የሠሩ አገልጋዮች ናቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ግብ ሰዎች በክርስቶስ እግዚአብሔርን እንዲያውቁ እና በእግዚአብሔር እውቀት ደግሞ የበሰሉ እንዲሆኑ ማድረግ ነው (**2 ጢሞቴዎስ 3፡14–17** ይመልከቱ)። ደግሞም ቅዱሳት መጽሕፍት የተጻፉት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማስተማርና ድፍረት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው **(ሮሜ 15፡4** ይመልከቱ)። እንደዚሁም በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ የጠቀሱት ታሪኮች ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዴት  መኖር እንዳለበት ምሳሌ እንዲሆኑ ታቅዶ ነው (**1 ቆሮንቶስ 9፡10፣ 10፤6** ይመልከቱ)። ስለዚህ ቅዱሳት መጽሕፍት ወንጌልን ነው የሚያስተምሩት (**1 ቆሮንቶስ 15፡3–4** ይመልከቱ)።

የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት **ቀስ በቀስ እያደገ እጨመረ** የሚሄድ ነው።[1] ይህ ማለት ደግሞ ቀደም ተብሎ የተጻፈው ክፍል አሁን ሐሰት ነው ወይም ደግሞ ቅርብ ጊዜ የተጻፍት ክፍሎች እውነተኛ ናቸው ለማለት አይደለም። ይልቁንም፣ ይህ ማለት በብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ  ክፍሎች ግልጽ ያልሆኑ ነገሮች በኋለኞቹ የቅዱሳት መጽሕፍ ክፍሎች የበለጠ ግልጽ በማድረግ ተብራርቷል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቀስ በቀስ እያደገ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ደግሞ እንደነ (**ማቴዎስ 5፡17–18፣ 11፡ 13–14፣ ዕብራውያን 11፡13** እና **1 ጴጥሮስ 1፡10–12**) የመሳሰሉትን ክፍሎች መመልከት ይቻላል።

---

[1] የዚህ ጽሁፍ ደራሲ እዚህ ጋ ለመግለጽ የፈለጉት በእንግሊዝኛው "Progressive" የሚለውን ሀሳብ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ **የሚታመን** ነው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል ሊሻር እንደማይችል መስክሮአል (**ዮሐንስ 10፡35** ይመልከቱ)። የእግዘአብሔር ቃል እውነት ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ የቃሉ ድራሲ ነውና እግዚአብሔር ደግሞ ሊዋሽ አይችልም (**ቲቶ 1፡2** ይመልከቱ)።

በጥንት ዘመን ሰዎች እምንታቸውን በእግዚአብሔር ላይ ያድርጉ የነበረው በተጻፉት ነገሮች ላይ ተመርኩዘው ነበር (**ኢያሱ 10፡13** ይመልከቱ)። ይህም ለእነርሱ እንደ ማረጋገጫ ሆኖ አገልግሏል። ይህ ሂድት ዛሬም ተመሳሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለምናምንበትና ስለምናደርገው ሁሉ መሠረታችን መሆን አለበት። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሪነት የሚያገለግሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ራሳቸውን መስጠት ይኖርባቸዋል።

ክርስቲያኖች ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት "**ሥልጣን**፣" "**ብቃት**" እና "**ግልጽነት**" መናገሩ ጠቃሚ እንደሆነ ተረድተዋል። **የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን** ማለት የእግዚአብሔር ቃል በሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ እምነትና ተግባር ላይ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው ማለት ነው (**መዝሙር 1፡119**፣ **2 ጢሞቲዎስ 3፡ 14–17** ይመልከቱ)። ደግሞም **የቅዱሳት መጻሐፍት ብቃት** ማለት እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በጥበብ በፊቱ እንድትኖር እና ሥራውንም እንድትሠራ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ **የሚያስፈልጉዋት ነገሮች ሁሉ** ሰጥቷታል ማለት ነው። እንግዲህ ለክርስቲያን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ የሆኑ ማንኛውንም ጽሑፎች አያስፈልገውም። ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሆነ ሌላ ነገር መፃፍ የሚያስፈልግ ቢሆን ኖሮ ይጻፍ ነበርና። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ማለት ግን ክርስቲያኖች ሌሎች መጻሕፍት አያንብቡ ማለትን አይደለም። ይልቁንስ ቅዱሳት መጻሕፍት በራሳቸው በቂ ናችው ለማለት ነው እንጂ። ስለዚህ ከሌሎች ጽሑፎች ምንም "እርዳታ" አያስፈልጋቸውም። ከሌሎች ጽሁፎችም እርማት አያስፈልጋቸውም። ይልቅስ ለሕይወት እና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር መልካም ቃል ውስጥ ይገኛሉና። **የቅዱሳት መጽሐፍት ግልጽነት** ማለት ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ሥልጠና በወሰዱ ሰዎች ብቻ የሚደረሱ ሚሥጥራት እንዲሆኑ የታሰቡ አይደለም ለማለት ነው። ይልቁንስ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት የእግዚአብሔርን መልካሙን ቃል ለመስማትና ለመታዘዝ የሚፈልጉ ሁሉ እንዲረዱት በሚያስችል መልኩ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉ። ሁለቱም ደግሞ የእግዚአብሔር እስትፋሳዊ ቃል ናቸው። ሁለቱም "ለማስተማር፣ ለመገሰጽ፣ለማቅናትና በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ" (**2 ቲሞቴዎስ 3፡16–17**)። የመጀመሪያው ክፍል ብሉይ ኪዳን ይባላል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሰላሳ ዘጠኝ መጽሕፍት ይገኛሉ፣ እነዚህም የተጻፉት ከኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በፊት ነው።


የሁለተኛው ክፍል ደግሞ አዲስ ኪዳን ይባላል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሃያ ሰባት መጻሕፍት ይገኛሉ፣ እነዚህ ደግሞ የተጻፉት ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሳኤ እና ዕርገት በኋላ ነው።

መረዳት ያለብን ነገር ቢኖር ኢየሱስ ክርስቶስ በመምጣቱ ምክንያት አሁን ብሉይ ኪዳን አስፈላጊ አይደለም ማለት አይደለም። እንዳውም ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ሐዋሪያት የተጠቀሙት በብሉይ ኪዳን የነበሩት መጻሕፍት ናቸው። በሌላ አገላለጽ ብሉይ ኪዳን የእነሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነበር ማለት ነው፣ ምክንያቱም በእነርሱ ጊዜ አዲስ ኪዳን አልነበረምና። በተጨማሪም ብሉይ ኪዳን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስም ነበር። አዲስ ኪዳን ገና እየተጻፈ ነበርና፣ እንደዚሁም የተለያዩ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ገና በመጽሐፍ ደረጃ አልተዘጋጁም ነበር! ዛሬ ግን ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን በነቢያት የተጻፉትን እና በአዲስ ኪዳን በሐዋሪያት የተጻፉትን በማግኘታቸው በረከት አግኝቷል። ለዚህም ነው **ኤፌሶን 2፡20** ቤተ ክርስቲያን “በሐዋሪያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻለች” የሚለው። በአዲስ ኪዳን ያሉትን ጽሑፎች ለማጠናቀቅ እግዚአብሔር ሐዋሪያትን ተጠቅሟል። የብሉይ ኪዳን ጽሑፎችን ለማጠናቀቅ ደግሞ እግዚአብሔር ነቢያትን ተጠቅሟል። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የሐዋሪያትን (አዲስ ኪዳን) እና የነቢያትን (የብሉይ ኪዳንን) ሥራ ታከብራለች። **በኤፌሶን 2፡20** ላይ ሐዋሪያት በመጀመሪያ ላይ መጠቀሳቸው ደግሞ የሚያመለክተው ትርጉምን ለመወሰን መጀመሪያ መመልከት ያለብን ሐዋሪያት መሆናቸውን ለማሳየት ነው። ይህም ማለት በሌላ አገላለጽ ሐዋሪያት የነቢያት ተርጓሚዎች ናቸው ለማለት ነው።

ሁለቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚናገሩት ስለ ክርስቶስና ስለ መንግሥቱ ነው (ለምሳሌ **ሉቃስ 24፡25–27፣ 24፡44–48፣ ዮሐንስ 5፡39–47፣ እና የሐዋሪያት ሥራ 3፡18–26** ይመልከቱ)። እንደዚሁም ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ክርስቶስ መሆናቸው ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት መጻሕፍት ሁሉ ሊሰበክ ይችላል ማለት ነው። ለዚህም ነው ሰባኪዎችና አስተማሪዎች የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን መጠቀም መማር ያለባቸው።


የሰባኪው ወይም የመምህሩ ሥራ ከጽሑፉ በስተጀርባ ያሉትን ክስተቶች ማወጅ አይደለም። ለምሳሌ ያህል የሰባኪው ወይም የመምህሩ ሥራ ዓለምን ያጥለቀለቀው የጥፋት ውሃ ጎርፍ ተፈጥሮአዊ ይዘት ምን እንደነበረ የጂኦሎጂ ጥናት በመመርመር ወዘተ ማስረዳት አይደለም። ይልቁንም የሰባኪ ወይም የአስተማሪ ሥራ መሆን ያለበት እራሱ የተጻፈውን ብቻ ማወጅ ነው።

በተለይም ትኩረት ማድረግ የሚያስፈልገው፣ ደራሲው እንዴት ነው የሚናገርው? ደራሲው አንዖት የሚሰጠው ስለምን ጉዳይ ነው? ጸሐፊው እውነት ነው የሚለው ምንድር ነው? የደራሲው አመለካከት ትክክለኛው አመለካከት ነው።




## 2. ብሉይ ኪዳን ምንድን ነው?

በብሉይ ኪዳን ውስጥ 39 መጽሐፍት ይገኛሉ። እነዚህ መጻሕፍት መጀመሪያ የተጻፉት በዕብራይስጥ ነው። እንደዚሁም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በግሪክ ቋንቋ ተተርጉመዋል። ከግሪክ ትርጉሞች ውስጥ በጣም ዝነኛ የሆነው አንዳንድ ጊዜ ሴፕቱጀንት (ወይም ደግሞ **LXX** በመባል ይታወቃል ምክንያቱም አንድ ታሪክ እንደ ሚያስረዳው ከሆነ የግሪኩን ትርጉም ለማጠናቀቅ **70 ያህል ሰዎች** ተሳትፈውበታል የሚል ነው)። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉንም ተጽፈው ያለቁት ከክርስቶስ መምጣት በፊት ነው። ከጽሑፎቻቸው እንደ ምንረዳው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን የጻፉ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንደነበራቸው ግልጽ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች ስለ ክርስቶስ ያውቁ ነበር፣ ስለ እርሱም እንደ ጻፉም ተገንዝበው ነበር። እንደዚሁም ደግሞ እነርሱ የሚጽፉት ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡት ሰዎች ጥቅም እንደሆነም ያውቁ ነበር (**1 ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ)። በሦስቱ ማለትም ሕግ፣ ነቢያትና መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን መጻሕፍት በመጨረሻ ቅደም ተከተላቸው መሠርት በማድረግ፣ ብሉይ ኪዳንን ወደ መጨረሻው አድርሶ በማጠናቀቅ ያዘጋጀውን ሰው ውይም ሰዎች እምነት እንደ ነበራቸው ግልጽ ነው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በኢየሱስ እና በሐዋሪያትም ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህ ብቻ ደግሞ አይደለም፣ ኢየሱስ እና ሐዋሪያቱ ከእነርሱ በኋላ የሚመጡት የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት እንዲጠቀሙ ይጠብቁ ነበርና (**2 ጢሞቴዎስ 3፡16–4፡1** ይመልከቱ)። እንደዚሁም ደግሞ ዛሬም ቢሆን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቤተ ክርስቲያን ትጠቀማለች ተብሎ ይጠበቃል። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲጠቅሱ፣ ይናገሩ የነበሩት ስለ ብሉይ ኪዳን ነበር ምክንያቱም አዲስ ኪዳን ገና አልተጻፈም ነበርና። ለዚህም ደግሞ አንድ ለየት ያለ ነገር አለ፣ ማለትም በ **2 ጴጥሮስ 3፡14–16** ሐዋሪያው ጴጥሮስ በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ አንዳንድ ጊዜ " በቀላሉ ለመረዳት የሚያዳግቱ ነገሮች" እንዳሉ እና "እውቀት የጎደላቸውና የማይረጋጉ ሰዎች እነዚህን ጽሑፎች እንደሚያጣምሙ" ተናግሮ ነበር። እደዚህ የሚያድርጉ ሰዎች ደግሞ "በሌሎቹ ቅዱሳን ጽሑፎች" እንደሆኑ በመናገር፣ ጴጥሮስ "ሌሎች ቅዱሳት ጽሑፎችን" በመጥቀስ የጳውሎስ ጽሑፎችም ቅዱሳት መጻሕፍት መሆናቸውን ገልጿል ማለት ነው።




## 3. አዲስ ኪዳን ምንድን ነው?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ 27 መጽሐፍቶች ይገኛሉ። እነዚህ መጽሐፍት መጀመሪያ የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ነበር። ደግሞም እነዚህ መጽሐፍት የተጻፉት ከክርስቶስ መምጣት በኋላ ነው። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብሉይ ኪዳንን በተደጋጋሚ ይጠቅሳሉ። ይህም ደግሞ  በብሉይ ኪዳን መልእክት እና በአዲስ ኪዳን መልእክት መካከል የጠበቀ ግኙኝነት መኖሩን ያስረዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት አንድ ትልቅ መጽሐፍ ነው። ኢየሱስ እና ሐዋሪያት በብሉይ ኪዳን የተጻፉትን ጽሑፎች እንዴት እንደተረጎሙ በጥንቃቄ ማጥናት ለሰባኪው ትልቅ አስተዋጻኦ ያደርጋል። ኢየሱስ ክርስቶስ እና ሐዋሪያት የብሉይ ኪዳንን ቅዱሳት መጻሕፍት በመረዳት ትክክለኛ መንገድ አስተምረዋል። ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ሐዋሪያትን እንደ ታማኝ መሪዎች እንድትመለከታቸው እንደሚፈልግ ግልጽ ነው (**ዮሐንስ 14፡25–31 እና 16፡12–15** ይመልከቱ)። ሰባኪው በዮሐንስ 14፡25–31 እና 16፡12–15 በተጻፈው የኢየሱስ ቃል መሠረት፣ ሐዋሪያት የብሉይ ኪዳንን ጽሑፎች ሲተረጉሙም ሆነ በብሉይ ኪዳን ደግሞ በግልጽ ያልተነገሩትን ነገሮች በሚያስተምሩበት ጊዜ ሁልጊዜ ትክክል እንድሆኑ እርግጠኛ መሆን ይችላል።



## 4. የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱም ክፍሎች ክርስቶስንና መንግሥቱን የሚመለከቱ ናቸው

ሁለቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች (ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን) ስለ ክርስቶስ እና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚተርኩ ናቸው (**1 ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ስለክርስቶስና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚተርኩት በተመሳሳይ መንግድ አይደለም። መጽሐፎቹ አንዱ ከሌላው በጣም የተለያዩ ናቸው።አንዳዶቹ ቀለል ያሉ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ከበድ ያሉ ናቸው። ቢሆንም ቅሉ ሁሉም መጠናት አለባቸው፣ ምክንያቱም ሁሉም ለእግዚአብሔር ስላላቸው ፍቅር እንደዚሁም እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሳድጉ የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲያውቁ ጠቃሚ ነገር ያበረክታሉና። አንዳንዶች መጻሕፍት ኢየሱስን በስም ይጠቅሱታል። ሌሎች ደግሞ አያደርጉትም። አንዳንዶች ድነትን እንዴት እንዳስገኘልን ይጠቅሳሉ። ሌሎች ደግሞ አያደርጉትም። የክርስቶስ ታሪክ ከእያንዳንዱ መጻሕፍት እንዴት እንደሚሰበክ ማየት የሰባኪው ደስታ እና ግዴታም ሊሆን ይገባል። ለምሳሌ ያህል የእግዚአብሔርን ስም ምንም የማይጠቅስ አንድ መጽሐፍ አለ፣ይህም መጽሐፈ (አስቴር) ነው። ሆኖም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባጣም አስፈላጊው ገፀ ባህሪ እግዚአብሔር መሆኑን ደራሲው አንባቢው እንዲያስትውል የሚፈልግባቸው ብዙ ፍንጮች ደግሞ አሉ! ስለዚህ እያንዳንዱ መጽሐፍ ለክርስቶስና ለእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ አስተዋጽኦ የሚያደርገው እንዴት እንደሆነ መገንዘብ የሰባኪው ደስታና ደግሞም ግዴታው ነው። ሌላው ምሳሌ ደግሞ የመሳፍንት መጽሐፍ ነው። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ያለ ፈሪሀ እግዚአብሔር ከሆነ ንጉሥ ጋር ሲኖሩ ምን እንደሚመስል ያሳያል። የመሳፍንት መጽሐፍ ክርስቶስን በስም አይጠቅስም ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ያሚገዛቸው ንጉሥ እንደሚያስፈልጋቸው ያሳያል። በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በዙፋን ላይ የሆነ ንጉሥ ባልነበረበት በመሳፍንት ዘመን ስለተከሰቱት መጥፎ ጊዜያት ማንበብ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር የመረጠው ንጉሥ እንዲገዛ ረሃብን መፍጠር ይኖርበታል። በተጨማሪም የመሳፍንት መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በእነርሱ ላይ የሚገዛ ጥሩ ንጉሥ ባይኖራቸው ምን ሊደርስባቸው እንደሚችል ማስጥንቀቂያ ይሰጣል። ዛሬ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በእነርሱ ላይ የሚነግሥ መልካም ንጉሥ ስላላቸው እንደሰታለን። ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (**ማቴዎስ 1፡1 እና 28፡18–20** ይመልከቱ)።



## 5. የብሉይ ኪዳን ሦስቱ ክፍሎች

ብሉይ ኪዳን ሦስት ክፍሎች አሉት፡ እነዚህም፤ ሕግ፣ ነቢያት፣ እና ጽሑፎች ናቸው (**ሉቃስ 24፡ 25–27** እና **44–47** ይመልከቱ)። ጽሑፎች ወይም ድርሳናት የሚባለው ክፍል አንዳንዴ መዝሙረ ዳዊት በመባል ይታወቃል። እነዚህ ሦስቱንም ክፍሎች የሚናገሩት ስለ ክርስቶስና ስለወንጌል መልዕክት ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ መጻሕፍት ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ክስተት በተመሳሰይ መንገድ አይተርኩም።

እንግዲህ በእንደዚህ ሁኔታ ውስጥ የተገለጠው መስቀል ደብዛዛ ነው ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ስለክርስቶስ እና ስለወንጌል መልእክት  የተነገረበት መንገድ እንደ አዲስ ኪዳን ግልጽ ባለመሆኑ ነው። ለምሳሌ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የክርስቶስን ስም ግልጽ አድርገው አይነግሩንም። ነገር ግን ይህንን እውነታ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በግልጽ ይነግሩናል። ሆኖም ምንም እንኳን መጻሕፍቱ እንደ አዲስ ኪዳን መጻሕፍት በግልጽ ስለክርስቶስ ባይናገሩም፣ የክርስቶስን ታሪክ እና የወንጌልን ክስተት ግን እንደሚናገሩ ማወቅ አስፈላጊ ነው (ለምሳሌ **ዮሐንስ 5፡39–47** ይመልከቱ)። ስለዚህ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ክርስቶስን እንዴት አድርገው እንደሚያውጁት መወሰን የሰባኪው ደስታና እንደዚሁም ግዴታ ሊሆን ይገባል።


አሁን በዚህ ዘምን የምንጠቀምበት መጻሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የመጻሕፍት ዝርዝር ቅደም ተከተል በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱ ወቅት ከነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ዝርዝር ጋር ሲነጻጸር ተመሳሰይ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ ኢየሱስና ሌሎች ቅዱሳን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉትን መጽሐፍት የተጠቀሙበት መንገድ ግልጽ ያደርግልናል ማለት ነው (**ሉቃስ 24፡25–27** ይመልከቱ)። በተጨማሪም የመጽሕፍ ቅዱስ ምሑራን ጥንታዊው የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝሮች ግኝት የበለጠ ግልጽ አድርጎታል። ከእነዚህ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ በጣም ጥንታዊ የሆነው Baba Bathra 14b (ባባ ባትራ 14ለ) በመባል ይታወቃል። በዚህ በባባ ባትራ 14ለ ውስጥ የሚታየው የመጽሐፍት ዝርዝር ኢየሱስና ሐዋሪያቱ ሊያውቁት ከሚችሉት የማጽሐፍት ዝርዝር ጋር አንድ ዓይነት ወይም በጣም ተመሳሳይ እንደሆነ ይገመታል። በዚያ ዝርዝር ውስጥ እና በመሳሰሉት ሁሉም የሕጉ መጻሕፍት በአንድ ላይ ተሰባስበው ይገኛሉ። በመቀጠልም ደግሞ ሁሉንም የነብያት መጽሐፍቶች በአንድ ላይ ተሳባስበዋል። በመጨረሻም፣ ሁሉንም የጽሑፍ መጻሕፍቶች ደግሞ አንድ ላይ ተሰባስበው ይታያሉ።


በ **ሉቃስ 11፡51** ላይ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት ጀምሮ በዜና መዋዕል እንደ ሚጠናቀቅ ኢየሱስ ሌላ ፍንጭ ሰጥቷል። በዚህ ጥቅስ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን የሞቱትን ሰማዕታት በማንሳት ይናግራል። ማለትም ሁሉንም ሰማዕታት ለማንሳት በመፈለግ እንዲህ ይላል “ከአቤል ደም ጀምሮ በመሰውያውና በቤተ መቅደሱ መካከል እስከ ፈሰሰው እስከ ዘካሪያስ ደም ድረስ” ይላል። አቤል

በዘፍጥረት የታየ የመጀመሪያው ሰማዕት ነው። ዛካሪያስ ደግሞ በዜና መዋዕል ውስጥ የመጭረሻው ሰማዕት ነው፣ እሱም ኢየሱስ በተጠቀመበት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጨረሻው መጽሐፍ ነበር። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ዝርዝር የኢየሱስ ትምህርት ዋና ነጥብ ባይሆንም ቅሉ፣ እዚህ ጋ ግን ያስተማረው ይህንኑ ነው።

በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች ስንመለከት፣ ሚልክያስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ ነው፣ ምክንያቱም ክስተቶች የተፈጸሙበት የጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት፣ ሚልክያስ በብሉይ ኪዳን ከተናገሩት ነቢያት የመጨረሻው ነቢይ ነው። ስለዚህ፤ በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተቀመጡት ባብዛኛው በጊዜ ቅደም ተከተል ነው ማለት ነው። በኢየሱስ ጊዜ በነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ሚልክያስ የመጨረሻው መጽሐፍ አልነበረም። በጽሑፎች ውስጥ ያሉትን ሁሉም ማጻሕፍት ከሚልክያስ በኋላ የመጡ ናቸውና።

በኢየሱስ ጊዜ በነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ዜና መዋዕል የመጨረሻው መጽሐፍ ነበር፣ ምክንያቱም ከጽሑፎች ውስጥ የመጨረሻው መጽሐፍ ነውና። ዜና መዋዕል ከጽሑፍ ክፍሎች አንዱ ስለነበረም ነው ከሌሎች መጻሕፍት ጋር በጽሑፎች ውስጥ ተቀምጦ የሚገኘው። በሌላ በኩል ከሳሙኤልና ከነገሥት አጠገብ አልነበረም ማለት ነው ምክንያቱም ያንን የብሉይ ኪዳን ክፍል የነብያት መጽሕፍት ተብሎ ይታወቅ ስለነበር ነው።






## 6. የአዲስ ኪዳን ሦስት ክፍሎች

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት 27ቱ መጻሕፍት በሦስት የተለያዩ ክፍሎች ይከፈላሉ፡- እነዚህም የታሪክ መጻሕፍት፣ መለዕክቶች እና የራዕይ መጽሐፍ ናቸው። የታሪክ መጻሕፍት ከኢየሱስ ልደት በፊት የነበረውን ሁናቴና ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ የነበረውን ክስተቶችና ወንጌል ደግሞ እስከ ሮማ ድረስ እንዴት እንደ ተሰራጨ ይተርካሉ። መለዕክቶች ደግሞ ለአብያተ ክርስቲያናት ወይም ለግለሰቦች የተጻፉ ደብዳቤዎች ናቸው። የራዕይ መጽሐፍ ደግሞ "ለሰባት አብያተክርስቲያናት" የተጻፈ ደብዳቤ ቢሆንም ቅሉ፣ ከሌሎች መለዕክቶች ለየት ያለ የጽሁፍ ዓይነት በመሆኑ ምክንያት ለብቻው እንደ አንድ ክፍል ይጠናል ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ መልዕክቶች ደግሞ በሁለት ይከፈላሉ፤ እነዚህም የጳውሎስ መልእክቶች እና "ካቶሊክ" (አጠቃላይ) መለዕክቶች ይባላሉ፣ ይሁን እንጂ በዚህ ትምህርት ግን መለዕክቶች እንደ አንድ ትልቅ ቡድን እንወስዳቸዋለን።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ሦስቱንም ክፍሎች ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል መልዕክት የሚተርኩ ናቸው። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ስለ ክርስቶስ እና ስለ ውንጌል ክስተት በግልጽ በመናግራቸው ምክንያት በእነዚህ ሦስቱ ክፍሎች ስለመስቀል የተነገረው ሁሉ ግልጽ ነው (ለምሳሌ **ማቴዎስ 1፡1** ይመልከቱ)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉት እነዚህ ግልጽ ጽሑፎች ደግሞ ብሉይ ኪዳንን እንድንረዳ ያግዙናል ምክንያቱም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ከብሉይ ኪዳን ደጋግመው በመጥቀስ ጽፈዋልና።

ማወቅ ያልብን ጠቃሚ ንገር ቢኖር፡- የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ስለ ብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ሲጽፉ "ቅዱሳት መጻሕፍት" ብለው ይጠሩዋቸው ነበር። እነሱ "ብሉይ ኪዳን" ብለው አይጠሩዋቸውም። ምክንያቱም አዲስ ኪዳን ገና አልተጻፈም ነበርና ብሉይ ኪዳንን ቅዱሳት መጻሕፍት ብለው ይጠሩ ነበር። ሐዋሪያት ብሉይ ኪዳንን እንዴት እንደተጠቀሙ ደግሞ መረዳት ጠቃሚ ነገር ነው፣ ምክንያቱም የእነርሱ ትርጓሜ በኛ አተረጓጎም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይገባልና።



## 7. የብሉይ ኪዳን ሦስት ክፍሎች

እስከ መጀመሪያው መዕተ ዓምታት አጋማሽ ድረስ መጻሕፍት ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው ምክንያት ኢየሱስ በመጽሐፍ መልክ የታተመ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅጂ አልነበረውም። እንደዚሁም ደግሞ ሙሉውን የብሉይ ኪዳን የብራና ጥቅልልም አልነበረውም፤ ምክንያቱም የትኛውንም ጥቅልል ሁሉንም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሊይዝ አይችልም ነበርና። ይሁን እንጂ ራሱ ከተናገረው እንደ ምንረዳው ከሆነ ስለመጽሕፍቶቹ በተለየ መንገድ ያስብ እንደ ነበረ ግልጽ ነው። ለምሳሌ በ**ሉቃስ 24፡44** ላይ ስለ ሕግ መጻሕፍት፣ ነቢያት እና መዝሙረ ዳዊት ተናግሯል። እንደዚሁም ደግሞ በ**ሉቃስ 11፡51** ላይ ባለው ክፍል የተናገረው በብሉይ ኪዳን ቀኖና ውስጥ የተጻፈው ዜና መዋዕል የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ እንደሆነ አድርጎ እንደወሰደ ያሳያል። ምናልባትም "ኢየሱስ በነበረብት ጊዜ በነበረው "መጽሐፍ ቅዱስ" ውስጥ የተካተቱት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከዚህ በታች የተመለከተው ዝርዝር ይመስል ነበር።

**የሕግ መጻሕፍት**፡– ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘፀአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኍልቁ፣ ኦሪት ዘዳግም።

**የነቢያት መጻሕፍት፡**– መጽሐፈ ኢያሱ፣ መጽሐፈ መሳፍንት፣ መጽሐፈ ሳሙኤል (1–2 ሳሙኤል በአንድነት የተዋሀኹዱ ነበሩ)፣ መጽሐፍ ነገሥት (1–2 ነገሥት በአንድንት የተዋኹዱ ነበሩ)፣ ትንቢተ ኤርሚያስ፣ ትንቢተ ሕዝቃኤል፣ ትንቢተ ኢሳይያስ፣ ደግሞም 12ቱ ነቢያቶች (ትንቢተ ሆሴ፣ ትንቢተ ኢዩኤል፣ ትንቢተ አሞጽ፣ ትንቢተ አብድዩ፣ ትንቢተ ዮናስ፣ ትንቢተ ሚኪያስ፣ ትንቢተ ናሆም፣ ትንቢተ እንባቆም፣ ትንቢተ ሶፎኒያስ፣ ትንቢተ ሐጌ፣ ትንቢተ ዘካሪያስ እና ትንቢተ ሚልክያስ)።

**ጽሑፎች**፡– መጽሐፈ ሩት፣ መጽሐፈ መዝሙር፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ መጽሐፈ ምሳሌ፣ መጽሐፈ መክብብ፣ ማሕልየ መሓልይ፣ ሶዎቃው ኤርሚያስ፣ ትንቢተ ዳናኤል፣ መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ዕዝራ/ነህምያ (በመጀመሪያ እነዚህ አንድ መጽሐፍ ነበሩ)፣ ዜና መዋዕል (1–2 በአንድነት የተዋሃዱ ነበሩ)።

# የዓለም ኃያላን


| | |
|---|---|
| ግብፅ | 3000 ዓክልበ – 1200 ዓክልበ |
| እሥራኤል | 1010 ዓክልበ – 1200 ዓክልበ |
| ሶሪያ | 870 ዓክልበ – 626 ዓክልበ |
| ባቢሎን | 626 ዓክልበ – 538 ዓክልበ |
| ፋርስ | 539 ዓክልበ – 323 ዓክልበ |
| ግሪክ | 323 ዓክልበ – 146 ዓክልበ |
| ሮማ | 146 ዓክልበ – አዲስ ኪዳን |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3000–1200 | 1010 - 930 | 870 - 626 | 626 - 539 | 539 - 323 | 323 - 146 | **146 -** አዲስ ኪዳን |

## 8. ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን በሚያካትቱት ዘመን የነበሩት የዓለም ኃያላን


መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ ይነግረናል (**ማርቆስ 1፡ 14–15** ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር መንግሥት በተቀባው ንጉሥ በኢየሱስ እና በደስታ ለእርሱ በሚገዙትና ትዕዛዛቱንም በሚያከብሩት ሕዝቦቹ  አማካኝንት እግዚአብሔር የሚገዛበት መንግሥት ነው። ክርስቶስ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም "የተቀባ" ማለት ነው። ደግሞም እንደዚሁም መሲህ የሚልው ቃል የተገኘው ከእብራይስጥ ሲሆን ትርጓሜውም "የተቀባ" ማለት ነው። ለዚህም ነው ኢየሱስ አንዳንዴ ኢየሱስ ክርስቶስ ውይም ክርስቶስ ኢየሱስ የተባለው። የኢየሱስ ስም በእግዚአብሔር የተቀባ መሆኑን ጎላ አድርጎ ያሳያል።

ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው የእግዚአብሄር መንግሥት ብቻ አይደለም፤ እንደዚሁም ደግሞ በመጽሕፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰ ንጉሥ ኢየሱስ ብቻም ደግሞ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘረዘሩት ክስተቶች ሁሉንም ማለት ይቻላል የተፈጸሙት በተለያዩ የዓለም ኃያላን መንግሥታትና በተለያዩ ነገሥታት የግዛት ዘመን ነው።ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የትኞቹ መንግሥታት በሥልጣን ላይ እንደ ነበሩ ማወቁ ጠቃሚ ነው። የዓለም ኃያላን በክርስቶስ በኩል ለእግዚአብሔር መንግስት ሥልጣን መገዛት ስለማይፈልጉ ከእግዚአብሔር ጋር ይዋጋሉ (**መዝሙር 2፡1–3** ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ብቸኛው ገናና መንግሥት የእግዚአብሔር መንግሥት የሚሆንበት ቀን ይመጣል (**ዳናኤል 2፡44–45** ይመልከቱ)። የባቢሎን ንጉሥ የዚህችን ምድር መንግሥታት ከተራራ በተፈነቀለ ድንጋይ የወደሙበትን ሕልም አይቶ ነበር። ድንጋዩ ክርስቶስንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚወክል ነው።


2100BC
930BC
605BC
515BC
1000BC
586BC
70AD
1400BC
723BC
950BC
538BC
3000–1200
1010 - 930
870 - 626
626 - 539
539 - 323
323 - 146
146 - አዲስ ኪዳን

## 9. ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን በሚያካልሉት ዘመን ውስጥ የተከናወኑ ዋና ዋና ክስተቶች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡት ክንውኖች ተረት አይደሉም። በእርግጥም በጊዜና በታሪክ ሂድት ውስጥ የተከሰቱ ነገሮች ናቸው። በዓለም ታሪክ ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተካተቱት ጊዜያት የተፈጸሙ ብዙ ጠቃሚ ክንውኖች አሉ። የእነዚህ አንዳንድ ክስተቶች ትክክለኛ ወቅት አይታወቅም። የአንዳንዶች የተከናወኑበት ውቅት ደግሞ ይታወቃል። ከዚህ በታች የተመለከተው የጊዜ መስመር ለሰባኪ የተወሰኑት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት የተጻፉበትን ***ዐውድ*** እንዲረዳ ሊረዳው ይችላል። ይህም በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ለመረዳት እና የእነዚያን ቃላት ትርጉም ለሌሎች ለማስረዳት ይጠቅማል።



የሜድትራንያን ባሕር
እሥራኤል
1000
3000 - 1200
1010 - 930
870 - 626
626 - 539
539 - 323
323 - 146
146 - አዲስ ኪዳን


## 10. በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ አስፈላጊነት

ከዘፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ሆኖ ቀርቧል። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ደግሞ ምድራዊ ንጉሥ እንዲነግሥላቸው መመኘታቸው ኃጢአት አልነበረም። በእርግጥም ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ጀመሮ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በእነርሱ ላይ የሚገዛ ምድራዊ ንጉሥ እንደሚያስፈልጋቸው ግልጽ ምልክቶች ነበሩ (**ዘፍጥረት 49፡8–12** እና **ዘዳግም 17፡14–20** ይመልከቱ)። በዘፍጥረት 49፡8–12 መሠረት ይህ ንጉሥ ደግሞ የሚመጣው ከይሁዳ ነገድ እንደሆነ ግልጽ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ የመሳፍንት መጽሐፍ በከፊል የተጻፈው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን የሚፈራ ንጉሥ በእነርሱ ላይ በማይነግሥበት ጊዜ የሚሆነውን ለማሳየት ነው(**መሳፍንት 17፡6፣ 18፡1፣ 19፡1፣ 21፡25** ይመልከቱ)። ሕዝቡ ግን እግዚአብሔርን የሚፈራ ንጉሥ ሳይሆን፤ ልክ እንደ ሌሎቹም አሕዛብ ሕዝቦች አይነት ንጉሥ ይፈልጉ ነበር። ስለዚህ ሳኦል የተመረጠውም በዚሁ መሠርት ነው። ሳኦል ከቁመቱ ዘለግታ የተነሳ ንጉሥ ይመስል ነበርና። ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው አልነበረም። በመሆኑም ልክ እንደ አዳም የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ሕዝብ "ንጉሥ" ሳኦል እግዚአብሔርን አልታዘዘም እናም በዚህ ምክንያት በሕዝቡ ሁሉ ላይ መከራ ወርዶባቸዋል (**1 ሳሙኤል 13፡ 8–14** እና **15፡ 10–12** ይመልከቱ)።

ዳዊት በእሥራኤል ላይ ንጉሥ እንዲሆን የእግዚአብሔር ምርጫ ነበር (**1 ሳሙኤል 13፡14**፣ እና **16፡1 ፣ 12–13** ይመልከቱ)። ዳዊት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1000 አካባቢ የነገሠ እውነተኛ ሰው ነበር። በ **2ኛ ሳሙኤል 7፡1–17** ባለው ክፍል እንደ ምንመለከተው ለዳዊት በጣም ጠቃሚ ቃል ኪዳን ተገብቶለታል። ይህም አንዳንድ ጊዜ **የዳዊት ኪዳን** ተብሎ ይታወቃል። ይህ የተስፋ ቃል ከዳዊት ልጆች አንዱ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ለዘላለም እንደሚቀመጥ እና እግዚአሔርም ከዚህ ልጅ ጋር እንደሚሆን እንደዚሁም ምሕረቱንም ፈጽሞ ከእርሱ እንደ ማያርቅ ይናገራል። በተጨማሪም ይህ ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፤ እግዚአብሔርም አባት ይሆንለታል።እንግዲህ ኢየሱስ "የዳዊት ልጅ" ተብሎ ተጠርቷል (**ማቴዎስ 1፡1** ይመልከቱ) ምክንያቱም እሱ ካዳዊት ዘር ነው የመጣው፤ ስለዚህ የዳዊት ዙፋን ወራሽ ነው። እግዚአብሔር የቀባው ንጉሥ በግሪክ **ክርስቶስ**፣ በዕብራይስጥ ደግሞ **መሲህ** ይባላል። እነዚህ ሁለት ቃላት አንድ ነገር ያመለክታሉ። አዲስ ኪዳን ደግሞ ሁለቱንም ቃላት ስለ ክርስቶስ እንደሆነ ይናግራል (**ዮሐንስ 1፡41 እና 4፡25** ይመልከቱ)። በአዲስ ኪዳን መጀመሪያ ላይ ሰዎች ኢየሱስን ይህ ክርስቶስ ይሆንን እያሉ ይገረሙ ነበር (**ሉቃስ 3፡15** ይመልከቱ)። ምክንያቱም ክርስቶስ እንደሚመጣ በብሉይ ኪዳን በተጻፈው መሠረት ያውቁ ነበርና። ይሁን እንጂ በወቅቱ ኢየሱስን እርሱ ክርስቶስ መሆኑን አልተረዱም ነበር። ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩት ተአምራቶች እርሱ ክርስቶስ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች ነበሩ (**ዮሐንስ 20፡**

**30–31** ይመልከቱ)። ሐዋሪያት በስብከታቸውም ሆነ በመልዕክቶቻቸው፣ ክርስቶስ የሚለውን የማዕረግ ስም ከኢየሱስ ስም ጋር "በማያያዝ" ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን አሳይተዋል። ለዚህም ነው ኢየሱስን "ኢየሱስ ክርስቶስ" (**የሐዋሪያት ሥራ 2፡38** እና **3፡6** ይመልከቱ) ወይም "ክርስቶስ ኢየሱስ" (**የሐዋሪያት ሥራ 24፡24** እና **ሮሜ 2፡16** ይመልከቱ) ብለው የሚጠሩት። ሐዋሪያት የኢየሱስን ስም በዚህ መንገድ በመጠቀም ክርስቶስን አግኝተነዋል እያሉ ያውጁ ነበር።ስለዚህ ሰዎች እርሱ ማን ሊሆን እንደ ሚችል ማሰብ አያስፈልጋቸውም፤ ምክንያቱም ሐዋሪያት የናዝሬቱ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንድሆነ በሥልጣን አውጀዋልና።




የሜዲትራንያን ባሕር
እሥራኤል
ይሁዳ
1000
930
3000 - 1200
1010 - 930
870 - 626
626 - 539
539 - 323
323 - 146
146 - አዲስ ኪዳን

## ፲. አንድ ሀገር የነበረው የእሥራኤል ሕዝብ ወደ ሁለት ቦታ መከፈሉ

በኃጢያት ምክንያት የእሥራኤል ሕዝብ ወደ ሁለት ሀገርነት ተከፋፈለ።ይህ የሆነው በዳዊት የልጅ ልጅ በሆነው በሮብዓም ዘመነ መንግሥት ጊዜ ነው (**1 ነገሥት 12** ይመልከቱ)። ይህም በ930 ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። እንግዲህ በዚያን ጊዜ "ሁለት" የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነበሩ፤ ማለትም የሰሜኑ መንግሥት እሥራኤል እና የደቡቡ መንግሥት ይሁዳ ነበሩ። በወቅቱ የዳዊት የልጅ ልጅ የሆነው ሮብዓም በደቡቡ ምንግሥት በይሁዳ ላይ ሲነግሥ ከዳዊት ጋር ዝምድና የሌለው ኢዮርባዓም የሚባል ሰው ደግሞ በሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥት ላይ ነገሠ። ቅሬታ ከሆኑቱ በስተቀር እነዚህ ሁለቱ ወገኖች እግዚአብሔርን በእውነት አላመለኩም። ሁለቱንም ሕዝቦች ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል። ይሁን እንጂ በይሁዳ ከዳዊት ጋር የሚዛመዱ ነገሥታት ያነግሡ ነበር። በሰሜኑ በኩል የነበረው የእሥራኤል ምንግሥት ግን ይህን አያደርጉም ነበር። ቤተመቅደሱ የነበረው በይሁዳ በኢየሩሳሌም ነበር። በሰሜኑ መንግሥት እሥራኤል ግን መቅደስ አልነበራቸውም። ስለዚህ የመጀመሪያው ንጉሥ (ኢዮርባዓም የተባለው ሰው) ሕዝቡ ወደ ደቡብ ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ እንዳያመልኩ ስለፈለገ በእሥራኤል በሰሜንና በደቡብ አቅጣጫ ሁለት የወርቅ ጥጃ አቁሞ በዚያ እንዲያመልኩ ያደርግ ነበር። ለሕዝቡም ሁለቱ የወርቅ ጥጆች እሥራኤላውያንን ከግብፅ ያወጡት አማልክት እነርሱ እንደሆኑ ተናገረ (**1 ነገ 12፡25–33** ይመልከቱ)። ይህም ደግሞ ታላቅ ኃጢአት ነበር። ምንም እንኳን ብዙ ነቢያቶች እየተነሱ ቢያስጠነቅቁዋቸውም እንደዚሁም እግዚአብሔር ብዙ ምሕረት ቢያደርግላቸውም ከዚህ ኃጢአት ግን ሊመለሱ አልቻሉም። በዚህም ምክንያት በጦርነት ድል ሆኑ ወደ ተለያየ ቦታ በስደት ተበታተኑ።


እንግዲህ አሁን ክርስቶስ የተከፋፈለውና የተሰባበረውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አንድ አድርጎ አቅርቦአል። ከአሁን በኋላ የተለያዩ መሪዎች አይኖራቸውም። እርሱ ብቻውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ንጉሥ ነውና (**ሕዝቅኤል 34፡23 ፣ 37፡22–28፣ እና ሆሴዕ 1፡11** ይመልከቱ)።



## 12. የነቢያት አገልግሎት

በኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ ነቢያትን ይልክ ነበር። ነቢያት ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ሕዝቡ ያደርሱ ነበር። ዋና ሥራቸውም ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ ነበር። ተዓምራት በሚያደርጉበትም ጊዜ ቢሆን ሕዝቡ የእግዚአብሔር መገኘት እደዚሁም ኃይሉን እንዲአስታውሱ ለማድረግ እና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ ፀጋን ለማምጣት ነበር። የነቢያቱ ዋና ሥራ ለግዚአብሔር ሕዝብ "የእግዚአብሔር ድምፅ" መሆን ነበር። ደግሞም የቃልኪዳን ሰዎች መሆናቸውን በማስታወስ ሕዝቡን ወደ ንሰሐ ይጠሩ ነበር። በተጨማሪም እግዚአብሔር ሕዝቡን ከኃጢአታቸውና ከጠላቶቻቸው ሙሉ በሙሉ ነፃ ስለሚያወጣበት ጊዜም ይናገሩ ነበር። ሚልኪያስ የመጨረሻው ነቢይ ነበር። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ400 አካባቢ አገልግሏል። ስለዚህም "የነቢያት ዘመን" ተዘግቷል እና "ነቢያት" የተባለው የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ተዘግቷል ማለት ነው። ነቢያት የጻፉት ስለ ክርስቶስ እንደሆነ ያውቃሉ። እንደዚሁም ደግሞ እነርሱ የሚጽፉት ከእነርሱ በኋላ ለሚኖረው ለወደፊት ሕዝብ ጥቅም መሆኑንም ያውቁ ነበር (**ማቴዎስ** 13፡17፣ **ሉቃስ** 1፡67–69፣ **ዮሐንስ** 8፡56፣ **ዕብራውያን** 11፡ 13 እና 1 **ጴጥሮስ** 1፡10–12 ይመልከቱ)።

ሙሴ የነቢያትን አገልግሎት በተመለከተ በ**ዘዳግም** 18፡15–22 ባለው ክፍል ገልጿል። በዚያ ክፍል በተለይም ስለ አንድ "ነቢይ" ተናግሯል። ይህም ደግሞ ስለክርስቶስ የሚናገር ትንቢት ነው (**የሐዋሪያት ሥራ** 3፡17–26 ይመልከቱ)። ክርስቶስ ከነቢያት ሁሉ በላይ ታላቅ ነው። የነቢያት ንግግርና ተግባራቸው እሱ የሚያደርገውንና የሚናገርውን የሚያንፀባርቅ ነበር። በመጀመሪያዎቹ የነቢያት ዘመን የነበሩት የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ የነቢያትን ድምፅ ይታዘዙ እንደነበረ ሁሉ በዚህም ዘመን ሰዎች ሁሉ ክርስቶስን መታዘዝ አለባቸው፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የተላከ "ነቢይ" ስልሆነ ስለእግዚአብሔርንም የመናገር ስልጣን አለው። እንግዲህ ክርስቶስን የማይሰሙ ሁሉ ይፈረድባቸዋልና።



የሜዲትራንያን ባሕር
እስራኤል
ይሁዳ

## 13. የእሥራኤል እና የይሁዳ ነቢያት

አንዳንድ ነቢያት በዋንኛነት የተሰጣቸው መልዕክት በእሥራኤል ውስጥ ለነበሩት ሰዎች የሚመለከት ነበር። ሌሎች ደግሞ በዋንኛነት መለዕክቶቻቸው ያቀረቡት በይሁዳ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ነው።(አንዳንዴም ደግሞ ነቢያት በሌሎች አገሮች ለሚኖሩ ሕዝቦች ይናገሩ ነበር)። ይሁን እንጂ የነቢያት የመጀመሪያ አድማጮች የነበሩት በእሥራኤል ወይም በይሁዳ የነበሩት ሰዎች ቢሆንም ቅሉ፤ በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖችም የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያትን ችላ ማለት አይገባቸውም። ነቢያት በጽሑፋቸው ለክርስቲያኖችም እየተናገሩ ነውና። ስለዚህ መልእክቶቻቸው በጥንቃቄ ሊጠኑት እና ሊታዘዙትም ይገባል። ነቢያት የጻፉት ከእነርሱ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ በእርቀት ያሉትን ሰዎች እንደሆነ ያውቁ ነብርና (1 **ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ)። ነቢያት ጽሑፎቻቸው ለእሥራኤል ወይም ለይሁዳ ሕዝቦች ብቻ እንዳልሆነም ደግሞ ያውቁ ነበር። ስለዚህ በሁሉም ሰዎች ሊነበቡ እና እነደዚሁም ሰዎች መለዕክቶቻቸውን ሊታዘዙት ይገባል ማለት ነው።

አንዳንድ ነቢያቶች ደግሞ የሚታወቁት በተናገሩትና ከዚያም ተጽፈው *በቃኖና* በተካተቱት ትንቢቶቻቸው ብቻ ሳይሆን በፈጸሙትም ድርጊት ነው። ለምሳሌ ያህል፣ኤልያስና ኤልሳዕ በእሥራኤል ውስጥ ትንቢት የተናገሩ ነቢያት ነበሩ። ነገር ግን ትንቢቶቻቸ በስማቸው በተጻፈ መጽሐፍ ውስጥ አልተመዘገበም። ይልቁንም የመጽሐፈ ነገሥት ታሪክ ጸሐፊ ሲጽፍ ያተኮረው በሥራቸው ላይ ነው። እንግዲህ ክርስቲያኖችም ሊያስቡበት የሚገባ ነገር ቢኖር ከስብከታቸው ይልቅ ተግባራቸው ላይ ሊሆን ይግባል ማለት ነው። ኤልያስና ኤልሳዕ አስፈላጊ ከሆኑባቸው ምክንያቶች አንዱ የክርስቶስ **ምሳሌ** መሆናቸውን ነው። ክርስቶስ ታላቁ ነቢይ ነው፣ ስለዚህ የነዚህ የሁለት ነቢያት አገልግሎት የክርስቶስ አገልግሎትን የሚያመለክት ደብዘዝ ያለ ነጸብራቅ እንዲሆን ታስቦ ነበር። እንደዚሁም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ ማድረግ ያለባትን ሥራ ነጸብራቅ ናቸው። ለሌሎች ነቢያት ደግሞ በተቃራኒው ነው። መልዕክቶቻቸው ከማንኛውም ከፈጸሙት ተግባር ይልቅ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የሚገኙት "ትንቢቶቻቸው" በጽሑፍ የቀረበውና "ነቢያት" በመባል የሚታወቁት ስም

እና በዋንኛነት ደግሞ መልዕክት ያቀረቡላቸው ሀገራት ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። (በሌላ በኩል ደግሞ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ "በጽሑፎች" ክፍልም መጽሐፍ የጻፉትም ሰዎች "ነቢያት" በመባል እንደ ሚታወቁ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ለመምሳሌ (**በሐዋሪያት ሥራ 2፡29–30**) ባለው ክፍል ዳዊት ነብይ ተብሏል። ይሁን እንጂ ነቢይ ቢሆንም የዳዊት ጽሑፎች ከሌሎች የነቢያት መጽሐፍት ጋር "በነቢያት" ዝርዝር ውስጥ አልተካተተም።

**የእሥራኤል ነቢያት**

አሞጽ

ሆሴዕ

ዮናስ

ናሆም

**የይሁዳ ነቢያት**

አብድዩ

ኢዩኤል

ኢሳይያስ

ሚኪያስ

ዕንባቆም

ሶፎኒያስ

ኤርሚያስ


ሕዝቅኤል – (ሕዝቅኤል በይሁዳ በነበረበት ጊዜ ነቢይ ሆኖ አላጋለገለም። ነገር ግን ወደ ባቢሎን ከመማረኩ በፊት በኢየሩሳሌም ካህን ሆኖ አገልግሏል። ሆኖም ወደ ባቢሎን ከተወሰደ በኋላ በ 597 ከክርስቶስ ልደት በፊት ለነቢይነት ተጠርቷል።)

**ከምርኮ በኋላ የተነሱ ነቢያት**

ሐጌ

ዘካሪያስ


ሚልክያስ




የሜድትራንያን ባሕር
እሥራኤል
ይሁዳ
723
1000
930
3000 - 1200
1010 - 930
870 - 626
626 - 539
539 - 323
323 - 146
146 - አዲስ ኪዳን


## 14. እሥራኤል ተሸነፈ ሕዝቡም ተበታተነ

ምንም እንኳን ኃጢአታቸው ቢበዛም ለሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥት ለ 200 ዓመታት ያህል እግዚአብሔር ምህረቱን አሳይቷል። በእነዚህ ጊዜያትም ውስጥ ሰዎች ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። ነገር ግን ነቢያትን ሊሰሙ አልወደዱም። ስለዚህ የሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥት በአሶራውያን ተሸንፎ በ723 ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ሌላ ተሰደዱ። ይህ መሰደድ እንደሚመጣ በ**ዘዳግም4፡25–28** ተነግሮ ነበር። ይህም መሰደድ ደግሞ “መበታተን” በመባል ይታወቃል (**2 ነገሥት 17፡7–23** ይመልከቱ)። ስለእግዚአብሔር ሕዝብ በአለም ዙሪያ ስለተበታተኑት 12ቱ ነገዶች የአዲስ ኪዳንም ጸሐፊዎችም ይናገራሉ (**ያዕቆብ 1፡1 እና 1 ጴጥሮስ 1፡1** ይመልከቱ)። የተበተኑትን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚመልሰው ደግሞ ክርስቶስ ነው (**ዘዳግም 4፡29–31** ይመልከቱ)።


የሜዴትራንያን ባሕር
እሥራኤል
ይሁዳ
ባቢሎን
605
1000
930
723
3000 - 1200
1010 - 930
870 - 626
626 - 539
539 - 323
323 - 146
146 - አዲስ ኪዳን

## 15. ይሁዳ ተሸነፈ ሕዝቡም ወደ ባቢሎን ተወሰደ

ምንም እንኳን እሥራኤላውያን በ723 ከክርስቶስ ልደት በፊት ተሸንፈው የተበታተኑ ቢሆንም ከእነርሱ ተምረው የደቡቡ የእሥራኤል መንግሥት ከኃጢአቱ አልተመለሰም። የንስሐ ጊዜያት እንኳን የተሰጣቸው ቢሆንም ቅሉ ሰዎች ግን ከኃጢአታቸው አልተመለሱም። ስለዚህ የደቡቡ የእሥራኤል መንግሥትም በ605 ከክርስቶስ ልደት በፊት በምርኮ ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። እንድዚሁም ቤተመቅደሱም በ 586 ከክርስቶስ ልደት በፊት ፍረሰ።


1000
930
723
605
586
3000–1200
1010 - 930
870 - 626
626 - 539
539 - 323
323 - 146
146 - አዲስ ኪዳን

## 16. የቤተ መቅደሱ መፍረስ

በሰሎሞን የተገነባው ቤተመቅደስ በ586 ከክርስቶስ ልደት በፊት ፈርሷል። ይህ ቤተመቅደስ አንዳንድ ጊዜ የሰሎሞን ቤተመቅደስ በመባል ይታወቃል። ስለዚህ ከዚያ በኋላ ሰዎች ለአምልኮ የሚመጡበት እና የኃጢአት ስርየት የሚያደርጉበት በእግዚአብሔር የተመረጠ ቦታ አልነበረም። ሰዎች በእግዚአብሔር ማደሪያ ውስጥ ማመለክ ሳይችሉ የቀሩበት ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አልነበረም። እንደዚሁም ደግሞ አዳምና ሔዋን ከኤደን ገነት በትባረሩበትም ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ክስተት ተከስቶ ነበር። ይሁን እንጂ የፈረሰው ቤተመቅደስ በ516 ተመልሶ ተገንብቶ ነበር። ይህ ቤተ መቅደስም ቢሆን በ 70 ዓመተ ምሕረት ፈርሶአል። ይህ አንዳንድ ጊዜ የሁለተኛው የቤተመቅደስ ዘመን በመባል ይታወቃል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ በኢየሩሳሌም የቤተመቅደስ ሕንጻ ባይኖርም ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚመጡበት በእግዚአብሔር የተቀደሰ ቤተምቅደስ ደግሞ አለ። ኢየሱስ ደግሞ የዚህ ቤተመቅደስ የማዕዘን ራስ ድንጋይ ነው። ሰዎችም ወደ እርሱ በመምጣት የኃጢአት ይቅርታን፣ ፈውስን እና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግን ያገኛሉ። እንግዲህ "በክርስቶስ ያሉት" ሁሉ የዚህ ቤተመቅደስ ግንባታ አካል በመሆን አብረው እየተገነቡ ነው (**ዮሐንስ 2፡18–22፣ ኢፌሶ 2፡18–22 እና 1 ጴጥሮስ 2፡4–8** ይመልከቱ)። ይህም እውነተኛው እና ደግሞም የመጨረሻው ቤተመቅደስ ከመሆኑም በላይ በጭራሽ የማይፈርስም ነው። ቀደም ብለው የነበሩት ሁሉም ቤተመቅደሶች የእውነተኛው የክርስቶስ መቅደስና እና የቤተክርስቲያን **ምሳሌ** ነበሩ። ይህም ማለት ልትመጣ ላለችው ለእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲአይን ጥላ ነበሩ ማለት ነው።


የሜዲትራንያን ባሕር
እሥራኤል
ይሁዳ
1000
930
723
605 586
538
3000 - 1200
1010 - 930
870 - 626
626 - 539
539 - 323
323 - 146
146 - አዲስ ኪዳን

## 17. ከምርኮ መመለስ

በ538 ዓመተ ከክርስቶስ ልደት በፊት በምርኮ ተወስደው የነበሩት ከምርኮ መመለስ ጀመሩ። ይህም ከምርኮ መመለስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ሀገራቸው እንደሚመልስ የገባው የተስፋ ቃል መፈጸም መጀመሩን የሚያበስር ቢሆንም፤ የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ሕዝብ መልሶ የማምጣት የተስፋው ሙሉ ፍጻሜ ግን አለነበረም (**ዛዳግም 4፡25–31 እና 30፡1–10** ይመልከቱ)። ሁሉንም ከእግዚአብሔር የተሰጡ ተስፋዎች ሙሉ በሙሉ እና በመጨረሻም በክርስቶስ ተፈጽሞአል (**የሐዋሪያት ሥራ 13፡32–33** ይመልከቱ)። በክርስቶስ ሕይወጥ፣ ሞት እና ትንሳኤ ምክንያት፤ የተበተኑት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ዛሬም እየተሰበሰቡ ነው። የመጨረሻው የእግዚአብሔር ሕዝብ በተሰበሰበ ጊዜ፤ ክርስቶስ ተመልሶ በመምጣት መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ ይመሠርታል።